# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 247466

ህዳር 27 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች ፡--ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡----- አቶ ገብረፃድቅ ገብረኪዳን ቀረቡ

ተጠሪ፡---------ፋና ብሮድካሲቲንግ ኮርፖሬት አክስዮን ማህበር ነ/ፈጅ መስፍን ተስፋዬ

መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ የቀረበዉ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ስህተት ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት ተደርጎ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጠ፡፡

**ዉሳኔ**

አመልካች ያቀረቡትም ቀደም ሲል በተሰጠዉ ፍርድ ላይ ተፈፀመ ስህተት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ይታረምልኝ ሲሉ የጠየቁትን ላይ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡

አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ላይ በግራ ቀኞችን መካከል ያለዉ ኪራይ ዉል ፀንቶ የሚቆየዉ ለአንድ አመት ከስድስት ወር ሲሆን መጋዘኑን ለማስተካከል የሁለት ወራት ተቀናሽ ተደርጎ የአራት ወራት ይከፈል ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኞችን ያለዉ የኪራይ ዉል የአንድ አመት ከስድስት ወራት ስለመሆኑ ገልፆ እያለ ዉሉ የተደረገዉ ለአንድ አመት ብሎ መወሰኑ ስህተት ስለሆነ ያልተከፈለኝ ቀሪ የአንድ አመት ኪራይ ብር 3,450,000.00 (ሶስት

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) ተጠሪ እንዲከፍለኝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ታርሞ ይወሰንልኝ ሲሉ ጠይቋል ፡፡ተጠሪ በበኩሉ አስተያየት እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ያቀረቡት አስተያየትም አጠር ባለመልኩ ሲታይ፡-አመልካች በተጠሪ ላይ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፈል በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 ያቀረቡት ጥያቄ የህጉን መንፈስ ያለተከተለ ሲሆን አመልካች እያነሱ ያለዉ ጥያቄ በፍርድ ቤት አፃፃፍ ስህተት ሳይሆን በእራሱ የአመልካች የአፃፃፍና የማስረዳት ዉስንነት እንደሆነ የሚታይ እንጂ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት በቃል ወይም በቁጥር አጻጻፍ ስህተት ላይ ባልታሰበና ባለማስተዋል በፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ ስህተት ወይም ጉድለት በሌለበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ እንደተፈፀመ ስህተት አድርገዉ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት እንዲታረም የጠየቁት ጥያቄ ተገቢነት የለዉም የሚል አስተያየት ሰጥቷል፡፡

እኛም የቀረበዉን የአመልካች አቤቱታ መርምረን እንዳየነዉ ሳይታሰብ የቀረ ተጨማሪ የአንድ አመት ኪራይ ክፍያ ብር 3,450,000.00 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) ተጠሪ እንዲከፍለኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ይታረምልኝ ሲሉ የጠየቁትን ጥያቄ በተመለከተ መልስ ስለሚሻዉ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ/ 208 መሰረት ሊታረሙ የሚገባቸዉ ምን አይነት ስህተቶች ናቸዉ ? የሚሉትን በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 153610 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸዉ ጉዳዩችን ስናይ በፍርድ ወይም በዉሳኔ ወይም በትዕዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ፣ ባልታወቀና ባልታሰበ የተዘለለ የቃል ስህተት ስለመሆኑ በተመለከተ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 236245 ላይ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር 208 መሰረት የሚታረመዉ ነገር የዉሳኔዉን ይዘት የማይቀይርና መሰረታዊ ያልሆኑ ባለማስተዋል የተፈጠረ የጽህፈት ወይም የቁጥር ጉድለቶች ብቻ ስለመሆናቸዉ አስገደጅ ዉሳኔ የተሰጠበት ሲሆን አሁን በእጃችን ባለዉ ጉዳይ አመልካች በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ይታረምልኝ ሲሉ የጠየቁት የአንድ አመት ቀሪ የኪራይ ክፍያ ብር 3,450,000.00 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) እንዲከፈላቸዉ በፍ/ስ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር 208 መሰረት የቀድሞ ዉሳኔ ይታረምልኝ ሲሉ ያቀረቡት አቤቱታ ሲታይ በቀድሞ ፍርድ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ፣ ባልታወቀና ባልታሰበ የተዘለለ የቃል ስህተት ሳይሆን አመልካች በጠየቁት ሁኔታ ቀሪ የአንድ አመት ኪራይ ክፍያ ብር 3,450,000.00 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) እንዲከፈል ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የቀድሞዉን ዉሳኔ ማረም ማለት የቀድሞዉን ዉሳኔ ይዘት የሚቀይር እና የፍ/ስ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር 208 የተደገገበትን ዓላማ የማያሳካ እና ተቀባይነት የሌለዉ በመሆኑ ከዚህ አኳያ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር 208 መሰረት ያቀረቡት ጥያቄ ከላይ በተጠቀሰዉን የሰበር አስገዳጅ ዉሳኔ በሚጥስ መልኩ ያቀረቡት አቤቱታ መሆኑን የተገነዘብን ስለሆነ አመልካች በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ቀደም ሲል የተሰጠዉ ዉሳኔ ይታረምልኝ ሲሉ የቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለዉም፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!